# የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ)

## ጋዜጣዊ መግለጫ

(ታኅሣሥ 9 ቀን 1999 ዓ/ም)

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) በተለያዩ የማኅበራዊ፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት ነክ ፖሊሲ ጉዳዮች ዙርያ ጥልቅ ጥናት በማድረግ ግኝቶቹን ለሕዝብ፣ ለሚመለከታቸው የመንግሥት ፖሊሲ አመንጪዎችና አስፈፃሚዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻዎች በሕትመትና በሕዝባዊ የውይይት መድረኮች አማካይነት የሚያሰራጭ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። ማጥመ መንግሥት የሚከተለው ያልተማከለ የልማትና የአስተዳደር (የዲሴንትራላይዜሽን) ፖሊሲ በአራቱ ዋና ዋና ክልሎች ውስጥ በወረዳ ደረጃ ምን ያህል እንደተገበረና በዚሁ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችንና የቀረቡ አማራጮችን የሚቃኝ፣ በኖርዌይ መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ መለስተኛ የምርመር ፕሮጀከት በመንደፍ ከሰኔ 1998 ዓ/ም ጀምሮ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ይህ ፕሮጀክት ሶስት ዘርፎች አሉት። እነዚህም፤

1. ከሽግግሩ ወቅት ጀምሮ ያልተማከለ የልማትና የአስተዳደር ሥርዓት ግንባታን ሂደት በሚመለከት በኢትዮጵያ ወስጥ እስከዛሬ የተደረጉ ዋና ዋና ጥናቶችን በመለየት ለቀጣይ ምርምር የሚረዳ የዋቢ ጥናቶች ዝርዝር ማዘጋጀት፣ የተደረጉትን ጥናቶች በመገምገም የሚያነሷቸውን ዋና ዋና ጭብጦችና ግኝቶቻቸውን ማሳወቅና በቂ ጥናት ያልተደረገባቸውን መስኮች ለቀጣይ ጥናት መለየት፣

2. ከአራቱ ዋና ዋና ክልሎች በተመረጡ የናሙና ወረዳዎች ውስጥ ፈጣን የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በፖሊሲው ትግበራ ሂደት ስለተገኘው ውጤት፤ስላጋጠሙ እክሎችና ጠለቅ ያለ ጥናት ስለሚያሻቸው ጉዳዮች ለይቶ ማወቅ፣

3. በነዚህ ጥናቶች ውጤት ላይ የሚወያይ የአንድ ቀን ዐውደ ጥናት በማዘጋጀት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻዎች በቀጣዩ የጥናት ፕሮግራም ቀረፃ ላይ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ ናቸው።

ከላይ በተገለፀው መሠረት የጥናት ጽሑፎቹ ግምገማ የተጠናቀቀ ሲሆን የዳሰሳ ጥናቱም ቀደም ሲል የዚህ ዓይነት ጥናት ባልተካሄደባቸው ለናሙና በተመረጡ ስምንት ወረዳዎች፣ ማለትም ከኦሮምያ ክልል በሙሎ ሱሉልታና በያያ ጉለሌ ወረዳዎች፣ በደቡብ ክልል በአላባ ልዩ ወረዳና በስልጤ ዞን፣ በአማራ ክልል በሜጫና በደራ ወረዳዎች፣ በትግራይ ክልል በክልተ አውላሎና በሰሀርተ ሳምረ ወረዳዎች እንዲሁም ከአዲስ አበባ አስተዳደር በአዲስ ከተማና በአራዳ ክፍለ ከተማዎች ውስጥ ተካሂዷል።

በነዚህ ጥናቶች ውጤት ላይ ለመወያየትና በቀጣይነት በዲሴንትራላይዜሽን ላይ ሊካሄድ በታሰበው የረጅም ጊዜ የጥናት ፕሮግራም ውስጥ ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ የምርምር አጀንዳዎች ላይ ሀሳብ ለመለዋወጥ ማጥመ የአንድ ቀን ዐውደ ጥናት ታኅሣሥ 10 ቀን 1999 ዓ/ም በግዮን ሆቴል አዘጋጅቷል። የዚህ አውደ ጥናት ተሳታፊዎች ተመራማሪዎች፣ የመንግሥት ፖሊሲ አስፈፃሚዎች፣ በተለይም የዳሰሳው ጥናት የተደረገባቸው ወረዳዎች ተወካዮችና ባለሙያዎች፣ የልማት አጋሮች ተወካዮችና ሌሎች አግባብ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው።

ማጥመ ከላይ የተገለፁትን ጥናቶች ውጤት በቅርብ ጊዜ ውስጥ በማሳተም ለሕብረተሰቡና ሌሎች ተጠቃሚዎች ያሰራጫል።